# የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት ለሕዝብ እና ለሀገር ደህንነት ልማት ያላቸው መሠረትነት

**አብዱልፈታህ አብደላህ ሸቤ**[1]


### *አህጽሮት*

*የሀገራችን የትምህርት እና የተቋም ግንባታ ሒደት ከሀገር በቀል ዕውቀቶች እና ከባሕል ተቋማት ጋር አስተሳስሮ መመልከት እና ማልማት መቻል ያስፈልገዋል። በእስካሁን "የዘመናዊነት ዕድገት እና ሥልጣኔ" ሒደታችን ያላስተዋልነው፣ ያላተኮርንበት እና የጎደለን አካሄድ ቢኖር ይህ ጉዳይ ነው። በብዙ መንገዶች "ዘመናዊነትን፣ ዕድገትን እና ሥልጣኔን" ወደ ሀገራችን ለማምጣት ሞክረናል፣ ብዙ ጥረናል፣ ለፍተናል፣ ብዙ ዋጋም ከፍለናል።ነገር ግን የራሳችንን ረስተን፣ ትተንና ንቀን ጥለን ነው በውጪው ላይ ያተኮርነው ወይም የተንጠለጠልነው።[2] ይህም በመሆኑ እስካሁን ወዳሰብነው እና ወደ ተመኘነው የውጤት ወይም የስኬት ደረጃ ላይ ልንደርስ አልቻልንም። አካሄዳችንን መርምረን ካላስተካከልን በስተቀር ለወደፊትም መድረሳችን ያጠራጥራል። በመሆኑም የትምህርት፣ የዕውቀት፣ የዘመናዊነት፣ የሥልጣኔ፣ የልማት፣ የተቋም ግንባታ ወ.ዘ.ተ ትክክለኛ አረዳድ፣ አተረጓጎም እና አተገባበር መልሰን መከለስ ያለብን ይመስለኛል።"የዘመናዊነት፣ የልማት እና የሥልጣኔ" ጠቃሚ እና አስፈላጊ ቃላትን ተጠቅመን ወዳልተፈለገ መንገድ ከገባን ጊዜ ጀምሮ ከትክክለኛው ወይም ከሳይንሳዊው የትምህርት፣ የዕውቀት፣ የዘመናዊነት፣ የልማት፣ የሥልጣኔ ወ.ዘ.ተ መንገድ እንደወጣን ይመስላል። ምክንያቱም እነዚህ ጠቃሚ እና አስፈላጊ ነገሮችን የፈለግናቸው ወይም እየፈለግናቸው ያለነው ከራሳችን፣ ከውስጥ፣ ከሀገር፣ ከሕዝብ፣ ከነባር የካበተ ዕውቀት ወ.ዘ.ተ ሳይሆን ከውጭ፣ ከሩቅ፣ ብዙ ዋጋ ከሚያስከፍለን ቦታ እና ሁኔታ ነው። መሆን የነበረበት የራሳችንን እያጠናን፣ እያለማን፣ እየተጠቀምን የውጭንም የመጨመር ሒደትና መንገድ መከተል ነበር። በሌላ አገላለጽ በእራሳችን መሠረት ላይ ቆመን የጎደለንን፣ የሌለንን፣ ከራሳችን ልናሳካው የማንችለውን ከውጭ ማምጣት ማለት ነው። ስለሆነም እስካሁን ባልሞከርነው፣ ንቀን በተውነው፣ ረስተን በጣልነው በራሳችን መንገድ ማሰብ፣ መሥራትና ውጤቱን መገምገም ያለብን ጊዜ ላይ እንገኛለን። ይህኛው መንገድ ወጪ ቆጣቢ፣ ማኅበራዊ ዋስትናው ሰፊ፣ ዘላቂ እና የተረጋጋ መሆኑ ይታወቃል። ይህንንም ግንዛቤ ይዘን የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት ለሕዝብ እና ለሀገር ደህንነት ልማት ያላቸው መሠረትነትን ለመዳሰስ እንሞክራለን።*


## 1 ቁልፍ ቃላት

**የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት** - ጥንታዊነት ያላቸው፣ ሕዝቦች በየራሳቸው እና በየአካባቢያቸው የፈጠሯቸው፣ የሕዝብ ሁለንተናዊ ደህንነት (Human Security) ስርዓቶች እና ተቋማት ማለት ናቸው።

**የሕዝብ ደህንነት** (Human Security) - አንድ ሕዝብ ወይም ሀገር ወይም የሰው ልጅ ለመኖር፣ ሕልውናውን ለማስቀጠል የሚያስፈልጉት መሠረታዊ ነገሮች ማሚያ ዕውቀት፣ ሥርዓት እና ተቋምን ያመለክታል።

**ወታደራዊ ኃይል** - በአጠቃላዩ ሕዝብን ባማከለው የደህንነት ዕሳቤ (Human Security) ሥርዓት ውስጥ አንዱ የብሄራዊ አቅም ማስፈጸሚያ መሳሪያ (Instrument of national power) ነው።

**ዘመናዊነት** - ከአሁናዊ ሁኔታ ጋር የሚሄድ፣ ከወቅቱ እና ከዘመኑ ጋር የሚስማማ፣ የሚሠራ፣ የሚሆን፣ ወደ ኋላ ያልቀረ፣ ወደ ፊት የሚያሻግር ማለት ነው። ዘመናዊነት በግድ አዲስ ከመሆን ጋር የተያያዘ አይደለም። አዲስ ሆኖ የማይሠራ፣ የማያገለግል እና የማይጠቅም ብዙ ነገር አለ። እንደዚሁም የቆዩ ሆነውም የሚጠቅሙ፣ የሚያገለግሉ፣ የዘመኑን ችግር የሚፈቱ አያሌ ነገሮች አሉ። ስለሆነም ዘመናዊነት ይበልጥ ከሚሻል፣ ከሚጠቅም ጉዳይ ጋር የተያያዘ እንጂ ከሥሪት ጊዜ ጋር የተያያዘ አይደለም።

**ዕድገት** - ዕድገት ሁለንተናዊ ነው። የምጣኔ-ሃብት፣ የሰው ልጅ አስተሳሰብና አሠራር፣ የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና መንፈሳዊ ዕድገቶችን ሁሉ የሚመለከት ነው። ነጠላ ዕድገት በራሱ ችግር እንጂ የሰው ልጅ ደህንነትን (Human Security) አያረጋግጥም።

---

[1] የሀገር በቀል ዕውቀቶችና የባሕል ሥርዓቶች ጥናትና ምርምር ከፍተኛ ባለሞያ፤ ethiopluralism@gmail.com

[2] ይድነቃቸው ከበደ እና ኢሳያስ አየለ፣ የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጲያ፣ ቅጽ 1፣ የፍሕና የሕግ ሥርዓት ኢንስቲትዩት፣ ገጽ 16፣ 2007

***ሥልጣኔ*** - በሁላቀፍ ይዘቱ የተሻለ፣ የሠለጠነ፣ የዳበረ፣ ያደገ፣ የተመነደገ ዕውቀትን፣ ቴክኖሎጂን፣ ሥርዓትን እና ተቋማትን ያመለክታል።

***መሠረትነት*** - መሠረት፣ መነሻ የሆነ፣ ለሚታየው (Tangable) ነገር ጥሩ መቆሚያ ሆኖ የሚያገለግል፣ የማይታይ (Intangable) ሆኖ ቋሚ ነገር ማለት ነው። የሚታየው ቤት ወይም ሕንፃ ቢሆን የማይታየው እና መሬት ውስጥ የተቀበረው መሠረት መሆኑን ከማስታወስ ጋር ይተርጎም።

## 2 የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት ማለት ምን ማለት ነው?

የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት ማለት ከውጭ ያልመጡ፣ በእኛው በሀገር ውስጥ ቀደምት አባቶችና እናቶች የተፈጠሩ፣ በመሆኑም የፈጠራ ባለመብትነታቸው ወይም ሃብትነታቸው የእኛው የሆኑ፣ የሕዝብ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አጠቃላይ ሠላምና ደህንነት ለመጠበቅ ታስበው የተዘጋጁ የአስተዳደር እና የሕግ ተቋማት ማለት ናቸው። ባሕላዊ ሕጎች የአንድን ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ የመስተጋብር ሥርዓት እና ተቀባይነት ባለው መልኩ ለማስተዳደር በማኅበረሰቡ የወጡ እና የሚተገበሩ አስገዳጅ ደንቦች ወይም ሕጎች ናቸው።[3] "ሥርዓት-ማኅበር" ማለት የሰዎች ስምምነት፣ አንድነት፣ ደንብ እና ሕግን ያመለክታል። ከትንሹ ዕድር እስከ ትልቁ የሀገር መንግሥት ድረስ የሚገኙ ተቋማት "ሥርዓት-ማኅበር" ተብለው ይገለፃሉ። የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት ብዙ መጠሪያ ሥሞች አሏቸው።

1. የሕዝብ ሥርዓት-ማኅበራት
2. የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት
3. የሀገረ-ሰብ ሥርዓት-ማኅበራት
4. የማኅበረ-ሰብ ሥርዓተ ማኅበራት
5. የሀገር በቀል የአስተዳደር፣ የሕግ እና የፍትሕ ስርዓቶች
6. "አካባቢያዊ የባሕል የመንግሥት ስርዓቶች"
7. የሀገር በቀል ወይም የባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት-ማኅበራት ወ.ዘ.ተ ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ።[4]

"የሕዝብ፣ የባሕል፣ የሀገረ-ሰብ፣ የማኅበረ-ሰብ፣ የሀገር በቀል" ወ.ዘ.ተ ቃላት እርስ በርሳቸው ተወራራሽና ተመጋጋቢ ናቸው። ሁሉም ከእኛነታችን ወይም ከሀገራችን ጋር የተያያዙ ሆነው ይገኛሉ። "ሥርዓት-ማኅበራት" "የሥርዓት-ማኅበር" ብዙ ቁጥር ነው። ነጠላው "ሥርዓት-ማኅበር" ሲሆን ብዙው "ሥርዓት-ማኅበራት" ይሆናል። እንደሚታየው በሁለት ቃላት ጥምረት የተመሠረተ ቃል ነው። እነርሱም "ሥርዓት" እና "ማኅበር" የሚሉት ናቸው።

"ሥርዓት" ማለት ነፃ ትርጉሙ ሥነ-ደንብ፣ ሥነ-ሥርዓት፣ ሥነ-አካሄድ ወ.ዘ.ተ ማለት ነው። "ማኅበር" ማለት ደግሞ ሥነ-ጥምረት፣ ሥነ-ስብስብ፣ ሥነ-አንድነት ወ.ዘ.ተ ማለትን ያመለክታል። ስለሆነም ሁለቱ ቃላት ሲገናኙ የሚሰጠው ጥሬ ትርጉም የመሰባሰብ ወይም የስብስብ ወይም የአንድነት ሥርዓት፣ ደንብ፣ ሕግ የሚለውን ስዕል ይሰጠናል። በመሆኑም ከትንሹ ከመንደር ዕድር ጀምሮ እስከ ሀገረ-መንግሥት ብሎም የአህጉር እና የዓለም ልዩ ልዩ ጥምረቶችና አንድነቶች "ሥርዓት-ማኅበር" ተብለው ይገለፃሉ።

የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓት-ማኅበራት በሀገራችን የአካዳሚክ ትምህርት ውስጥ የሚገባቸው አረዳድ፣ አተረጓጎም እና አገላለጽ ገና አላገኙም። "ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች" በሚል ሥያሜ ጎልተው ይጠቀሳሉ። ነገር ግን ይህ አረዳድ፣ ሥያሜና አገላለጽ ተገቢነት የሌለው እንደሆነ ጥናቶቻችን ያረጋግጣሉ። ምክንያቱም "ግጭት መፍታት" ከሥርዓት-ማኅበራቱ አያሌ ተግባራት ውስጥ አንዱ ሥራና ተግባር ብቻ በመሆኑ ነው። "ግጭት መፍታት" የሥርዓት-ማኅበራቱን ሁለንተናዊ ይዘትና ተግባር የሚገልጽ እና የሚያሳይ አይደለም።

---

[3] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 19

[4] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የሀገረ-ሰብ የአስተዳደር ሥርዓቶች ለሀገር-ግንባታ ያላቸው መሠረትነት፣ በደብረ-ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሐዲስ ዓለማየሁ የባሕል ጥናት ተቀም 8ኛ የጥናትና ምርምር ዓመታዊ ኮንፈረንስ የቀረበ ጥናት፣ ከግንቦት 7-8/2013

ሥርዓተ-ማኅበራቱ በየአካባቢያቸው የሕዝብ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አጠቃላይ ጉዳዮችን እና ደህንነትን የሚመሩና የሚቆጣጠሩ ነበሩ።[5] መታወቅ እና መገለጽ የሚገባቸው በእነዚሁ አጠቃላይ ቅርጽ እና ይዘታቸው ማሳየት በሚችል ደረጃ መሆን ሲገባው ከብዙ ተግባሮቻቸው ነጥሎ በአንዱ ብቻ ሊሆን እንደማይገባ ጥናቶች ያመለክታሉ።[6] በዘርፉ ጥናቶች ያካሄዱ ባለሙያዎች እንዳረጋገጡት ሥርዓተ-ማኅበራቱ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ የሕይወት ዘርፎች ሁሉ ገዢ ሕግ፣ ሥርዓት እና ተቋም እንደነበሩ ነው።[7]

እስካሁን ባለን መረጃ ከአንድ መቶ በላይ የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት በሀገራችን መኖራቸው ይታወቃል።[8] በሌላ አገላለጽ ከአንድ መቶ በላይ የሆኑ ለሕዝብ እና ለሀገር ደህንነት መጠበቂያና ማስጠበቂያ መሠረት ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ሥርዓተ-ማኅበራት አሉን ማለት ነው። የቁጥራቸው መብዛት እንደ መልካም አጋጣሚ ቆጥሮ በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ለሁሉም የተፈጥሮ ሥነ-ምህዳር አካባቢ (ደጋ፣ ወይና-ደጋ እና ቆላ) ኑሮና ሕይወት አንድ ዓይነት ወይም ጥቂት ሥርዓተ-ማኅበራት ብቻ ሊያገለግሉ እንደማይችሉ ይታወቃልና ነው።[9] እንደ ተፈጥሮ ሥነ-ምህዳሩ አካባቢ የችግሮች ዓይነት እና የመፍትሔው መንገድ ስለሚለያይ ሥርዓተ-ማኅበራቱ በዛው ልክ የአማራጭ ዕውቀትና መንገድ ያዳበሩ ሆነው ይገኛሉ። ስለሆነም እንደ ተለያዩ የዕውቀት ተቋም (ዩኒቨርሲቲዎች) በመቁጠር ማጥናትና መጠቀም ያስፈልገናል።

በሀገራችን ከሚገኙ ከአንድ መቶ በላይ የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት የተወሰኑትን በሥም መጥቀስ ያስፈልገናል። መድ-ዓ (በአፋር)፣ ገዳ (በኦሮሚያ)፣ ሕግዳባ (በትግራይ)፣ ሔር-ሶማል (በሶማሌ)፣ የአባቶች ሥርዓት (በአማራ)፣ የጎርደነ-ሜረ/ራ (በማዕከላዊ ደቡብ ኢትዮጲያ)፣ ወይት-ሽሚርነይ (በአገው ሕዝብ)፣ ደሬ-ዎጋ (በጋሞ)፣ ምክረቾ (በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ)፣ የሲዳማ-ሜራ፣ ሀዲይ-ሜራ፣ የወላይታ-ሜራ ወ.ዘ.ተ እያለ ይቀጥላል። ከአንድ መቶ በላይ የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት በሀገራችን ይገኛሉ የተባለው በዚህ መልኩ በመቁጠር ነው።

የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት በቋንቋ እና በተፈጥሮ አካባቢ ልዩነቶች ምክንያቶች ሥያሜአቸው፣ አደረጃጀታቸው እና አሠራራቸው ቢለያይም በመሠረታዊ ፍልስፍና ደረጃቸው ተመሳሳይ፣ ተቀራራቢ እና ተመጋጋቢ የሆኑ ናቸው። በኢትዮጲያ ያሉት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በአፍሪካ ደረጃ የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት የሚቀራረቡና የሚመሳሰሉ እንደሆኑ ምሁራን ያስረዳሉ።

*"የአፍሪካን (የባሕል) ሕጎች በአንድ ማዕቀፍ ውስጥ ማስቀመጥ እንደሚቻል ይታመንበታል። የተወሰኑ አነስተኛ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው የአፍሪካውያን ባሕላዊ ሕጎችን የሚያመሳስላቸው አልያም ተቀራራቢ የሚያደርጋቸው የሥነ-ሥርዓት ደንቦች፣ መርሆዎች፣ ተቋማትና ሒደቶች አሉ። በመሆኑም የአፍሪካውያን ሕጎች ከሌሎች የሕግ ስርዓቶች የሚለዩባቸው የጋራ ባሕሪያት አሉ። ይህም የአፍሪካውያን እና የአውሮፓውያን ሕግ ብሎ ለመለየት በቂ ሊሆን ይችላል"።*[10]

## 3 የሀገር በቀል ሥርዓተ-ማኅበራት ለሕዝብ እና ለሀገር ደህንነት ያላቸው መሠረትነት

የሀገራችን ሕዝብ እና የሀገረ-መንግሥት ሥርዓት ተቋም ከዓለም ቀደምት መሆናቸው በሳይንስ እና በባሕልም የተረጋገጠ ነው። የሰው ልጅ በአካሉና በአዕምሮው ዳብሮ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት፣ በምድር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው፣ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ፣ በታላቁ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በኢትዮጲያ መሆኑ በዓለም የቅድመ ታሪክ ተመራማሪ ምሁራን እና በዩኔስኮ ከተረጋገጠ ቆይቷል።[11] ይህ እውነታ በሀገር በቀል ዕውቀቶችና በባሕል ሥርዓቶቻችንም የሚታወቅና የሚታመን ነው። በተለይም በሀገራችን የኩሽ ሕዝብ እና ሥርዓተ-ማኅበራት ውስጥ ዕውቀቱና እምነቱ ጠንካራ ሆኖ እናገኘዋን። ለምሣሌ የአፋር

---

[5] Alula Pankhurst and Getachew Assefa, Grass-roots Justice In Ethiopia, The Contiribution of Customary Dispute Resolution, Page 3, 2008

[6] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ ሔራ (የሀረሪ ሕዝብ የባሕል ሕግ ሥርዓት)፣ ገጽ 22፣ 2008

[7] ገብሬ ይንቲሶ፣ ፈቃደ አዘዘና አሰፋ ፍስሃ፣ ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጲያ፣ የኢትዮጲያ የግልግል ዳኝነት የማስማማትና ዕርቅ ማዕከል፣ ገጽ11፣ 2004

[8] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የሀገረሰብ የአስተዳደር፣ የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓቶች በኢትዮጲያ፣ ቅጽ 1፣ ሐምሌ/2010

[9] ፕሮፌሰር መብራቱ፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ፣ ለዘላቂ ሀገራዊ መፍትሔ፣ ከገጽ 19-23፣ የካቲት/2013

[10] ይድነቃቸው ከበደ እና ኢሳያስ አየለ፣ የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጲያ፣ ቅጽ 1፣ የፍሕና የሕግ ሥርዓት ኢንስቲትዩት፣ ገጽ 22፣ 2007

[11] ፕ/ሮ ላጲሶ ጌ ድሌቦ፣ የኢትዮጲያ የታሪክ መነሻና ሒደት ከዘመነ ሜጋሊቲዝም እስከ ሪፐብሊክ፣ ከ15,000 ዓ.ዓ እስከ 2000 ዓ.ም፣ ገጽ 24፣ 2008

መድ-ዓ፣ የኦሮሞ ገዳ እና የጋሞ ደሬ-ዎጋ ሥርዓተ-ማኅበራት ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። ሦስቱም ሕዝቦች እና ሥርዓተ-ማኅበራት የአደም እና ሐዋ ወይም የአዳም እና ሔዋን የመጀመሪያ ዝርያዎች ነን ብለው ያምናሉ።[12]

ከዚህም የሳይንስ እና የሀገራችን ባሕሎች ዕውቀትና እምነት በመነሳት የሀገራችን ሕዝብ እና ሥርዓተ-መንግሥት ከዓለም ቀደምት መሆናቸውን መገንዘብ ይቻለናል። የባሕልና እስፖርት እንደዚሁም የቱሪዝም ሚኒስቴሮች "ኢትዮጲያ ምድረ-ቀደምት" (Land of Origins) የሚል ሎጎ ፈጥረው መጠቀም የጀመሩት ከዚሁ ግንዛቤ በመመሳት መሆኑ ይታወቃል። በጎግል ውስጥ "Land of Origins" ብለው ቢፈልጉ የሚመጣው ይኸው ምድረ-ቀደምትነታችን ነው።

ይህም ከዓለም ቀደምት የሆነው የሀገራችን ሕዝብ እና ሀገረ-መንግሥት ሁለንተናዊ ሠላምና ደህንነት ሲጠበቅ፣ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የዘለቀው በሀገር በቀል ወይም በባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት ብቸኛ መሠረትነት እና አገልግሎት ሰጪነት ነበር። በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከውጭ ያመጣናቸው የሀገር መከላከያ፣ ፖሊስና ሌሎች የሀገር ሠላምና ደህንነት መጠበቂያ ተቋማት እስኪተኳቸው ድረስ ለብዙ ሺህ ክፍለ ዘመናት የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት (Human Security) ተቋማት ሆነው አገልግለዋል።

የሕዝብ ደህንነት (Human Security) ከላይ በቁልፍ ቃላት መፍቻ ገጽ ላይ እንደተገለጸው አንድ ሕዝብ ወይም ሀገር ለመኖር እና ሕልውናውን ለማስቀጠል የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ማሟያ ዕውቀት፣ ሥርዓት እና ተቋምን ያመለክታል። የሰው ልጅ ለመኖር ማኅበራዊ፣ ምጣኔ-ሃብታዊ እና አስተዳደራዊ ደህንነቶች ያስፈልጉታል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ቢጎደል ሕልውናውን ጠብቆ ከዘመን ወደ ዘመን ለመሸጋገር አይችልም። ስለሆነም የሀገራችን ሕዝብ ከተፈጠረ ጀምሮ (የዓለም ቀደምት ሕዝብ መሆኑን ከማስታወስ ጋር) እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን በብቸኝነት፣ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ከአዲሶቹ የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት ተቋማት ጋር በአጋርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

የሕዝብ ደህንነት ለዘላቂ ልማት መሠረታዊው ነገር ነው። በምዕራባውያን አረዳድና አተረጓጎም የሕዝብ ደህንነት (Human Security) በሰባት እንደሚከፈል ያትታሉ። እነርሰም፦

1. አስተዳደራዊ ደህንነት
2. ማኅበራዊ ደህንነት
3. ምጣኔ-ሃብታዊ ደህንነት
4. የጤና ሕይወት ደህንነት
5. የምግብ ደህንነት ወይም ዋስትና
6. የአካባቢ ደህንነት
7. የግለሰብ ደህንነት ናቸው።[13]

የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት እንዴት የሕዝብ እና የአካባቢያቸው ሠላምና ደህንነት ሲጠብቁ እንደነበር አራት የናሙና ማሳያዎችን በማንሳትና በማውሳት መመልከት ይቻለናል።

## 4 ማሳያ አንድ - መድ-ዓ (የአፋር ሕዝብ የባሕል ሥርዓተ-ማኅበር) የሕዝብ ደህንነት ተቋም

በአፋር ሕዝብ ሁለንተናዊ የኑሮ ወይም የሕይወት ዑደቱ የተመሠረተውና የሚመራው በመድ-ዓ ባሕላዊ ሥርዓተ-ማኅበር አማካኝነት ነው። በዘመናችንም የሕዝቡ አብዛኛው የኑሮ መሠረቱ ከዚሁ ባሕላዊ ሥርዓተ-ማኅበሩ ጋር የተሳሰረ ሆኖ እናገኘዋለን። የአፋር የመድ-ዓ ሥርዓተ-ማኅበር የሕዝብ ደህንነት መጠበቂያ የሚከተሉት መዋቅራዊ አደረጃጀቶች አሉት። እነርሱም፦

1. **መድ-ዓ ሀቦብቲ** - ሡልጣን (የሥርዓቱ ዋና መሪ) እና ኬዶ-ሀቦብቲ (የጎሣ አባቶቸችን በአባልነት የሚይዝ የመድ-ዓ ሥርዓት ዋናው ምክር ቤት ማለት ነው። ይህም ምክር ቤት ሕግ የማውጣት፣ የማሻሻል፣ የመሻር እና የመቆጣጠር ሥልጣን የያዘው ነው። በዘመናችን እንደ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (Legislative) ዓይነት ሆኖ ይታያል። የሕዝቡ ማኅበራዊ፣ ምጣኔ-ሃብታዊ እና ፖለቲካዊ ሕይወት የሚቀመረውና የሚወሰነው በዚህ ምክር ቤት ውስጥ ነው።

---

[12] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ መድ-ዓ (የአፋር ሕዝብ የባሕል ሥርዓት)፣ ገጽ 201፣ ሰኔ/2000

[13] Shahrabanou Tadjbakhsh and Anuradha M. Chenoy, Human Security concepts and implications, 2007

2. **ባሮህ-ኢዶላ** (Barro Eddolla) - ይኸኛው ክፍል የሕግ ተርጓሚ (Judiciary) ሆኖ የሚያገለግለው ነው። በመድ-ዓ ሀቦብቲ ሥር ሆኖ በየአካባቢው የሚነሱ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን የመዳኘትና የመፍታት አገልግሎት ይሰጣል። ማኅበራዊ፣ ምጣኔ-ሃብታዊና ፖለቲካዊ ሠላምና ደህንነቶች ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና እና ድርሻ ያለው አካል ሆኖ እናገኘዋለን።

3. **ፊዕማ** (Fiema) - ፊዕማ የሕግ አስፈፃሚውን (Excutive) ክፍልን ያመለክታል። ከላይ ባሉት ተቋማት እየታገዘ እና የራሱን ነፃና የተሟላ ተቋማዊ አደረጃጀት በመጠቀም የሕግ እና ሥርዓት ማስከበር ሥራውን ይሠራል። ሕዝቡን ከውስጥና ከውጭ አደገዎች የመጠበቅ ኃላፊነት የሚወጣው ይኸው ክፍል ነው።[14]

የፊዕማ ተቋዊ ጥንካሬ እንደ ቀድሞ ባይሆንም አሁንም በአፋር ሕዝብ የሕልውና ጥያቄ ጉዳዮች ዙሪያ ወሳኝ ሚናዎችን በመጫወት ላይ ይገኛል። በሠላማዊ ጊዜ ለውስጥ አገልግሎት (ለማኅበራዊና ምጣኔ-ሃብታዊ ልማት)፣ ሠላም በሚደፈርበት ወቅት ደግሞ የጦርነት ሥራና ተግባሩን ያከናውናል። ለምሣሌ ከ2012-2014 በነበረው የሰሜን ኢትዮጲያ የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ የፊዕማ ተቋም ሚና ከፍተኛ እንደነበር ይነገራል። የፊዕማው ተቋም ከክልሉ ሚሊሻ እና ከኢ.ፌ.ድ.ሪ መከላከያ ሠራዊት ጋር ሆኖ እያንዳንዱን መንደር እና ቀበሌን ደህንነት በመጠብቅ ምትክ የሌለው የሠላምና ደህንነት ሥራ መሥራቱ ይገልፃል።

በአጠቃላይም ሦስቱ ዋና ዋና የመድ-ዓ ሥርዓት ተቋማት ማለትም መድ-ዓ ሀቦብቲ (ሕግ አውጪው ክፍል)፣ ባሮህ-ኢዶላ (ሕግ ተርጓሚው) እና ፊዕማ (ሕግ አስፈፃሚው) እጅግ በተቀናጀ ሁኔታ የአፋርን ሕዝብ እና አካባቢ ለብዙ ክፍለ ዘመናት ደህንነት ሲጠብቅ ኖርዋል። በአፋር የበረሃ የአየር ፀባይና ምድር ውስጥ የሰው ልጅ እንዴት ሕልውናውን ጠብቆ ሊኖር እንደሚችል የሚያሳይ ብልሃት፣ ዕውቀት፣ ጥበብ፣ በአጠቃላይም ሥርዓት ሆኖ ይገለፃል። የመድ-ዓ ሥርዓት ከአፋር ሥነ-አካባቢያዊ ተፈጥሮ አንፃር ሥነ-አስተዳደሩን፣ ሥነ-ማኅበራዊ ሳይንሱን፣ ሥነ-ኢኮኖሚያዊ ዘርፉን፣ የሥነ-ጤና አገልግሎቱን፣ የምግብ ደህንነቱን፣ የአካባቢ ጥበቃውንና ልማቱን ወ.ዘ.ተ በአስተማማኝ ሁኔታ ሲመራ ኖሯል፣ አሁንም የድርሻውን በመወጣት ላይ ይገኛል።

የአስተዳደራዊው የሕዝብ ደህንነት ዘርፉ በመድ-ዓ ሀቡብቲ፣ በባሮህ-ኢዶላ እና በፊዕማ ቀጥተኛ አመራር ይከናወናል። የማኅበራዊ ክፍሉም የመድ-ዓ ሥርዓት ባስቀመጠው መሠረተ ፍልስፍናውን፣ ዓላማውንና አሠራሩን ይዞ ይራመዳል። ለምሣሌ ኢብናይቲኖ (የእንግዳ አቀባበል)፣ ሀራይና-ኩራ (የደስታና የሀዘን መደጋገፍ)፣ እድቦንታ (በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን መልሶ የማቋቋም ተግባር)፣ ሙጋኢና (ዝምድናውን በተመኙት ሰው ሥም የልጅ ሥም መሰየምና ማሳወቅ)፣ ፍራንጋኢና (ከወላጆች በተጨቸማሪ ሌላ ወላጆችን መጨመር)፣ ዓላ (በግለሰቦች መሀከል የሚፈጠር ዘላቂ ወዳጅነት መመሥረት)፣ አፌሂና (በጎሣዎች መሀከል የሚቋቋም ዘላቂ ወዳጅነት) እና በመሳሰሉት አሠራሮች፣ ልምዶች፣ ዕውቀቶችና ማኅበራዊ ተቋት ይመራል።[15]

የምጣኔ-ሃብቱም ዘርፍ በአካባቢው ሊመረትና ሊረባ ከሚችለው የሰብሎችና የእንስሳት ሃብቶች ጋር ተያይዞ ዕውቀቱ፣ ልምዱና ሥርዓቱ በመድ-ዓው አስተናባሪነት ይለማል። አርብቶ አደርነት ዋንኛው የአፋር የምጣኔ-ሃብት ሙያ ዘርፍ በመሆኑ በዚህ ዘርፍ የተለዩ ዕውቀቶች፣ አሠራሮች፣ ልምዶችና ስርዓቶች ይገኛሉ። ከቤት እንስሳት ልማት ጋር ብቻ ሳይሆን በተያያዥ ጉዳዮች የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ (ሣርና ውሃ)፣ የዱር እንስሳት እና በሌሎች ዙሪያም የመድ-ዓ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓቱ ለየት የሚሉ ዕውቀቶች፣ ልምዶች፣ አሠራሮች፣ ስርዓቶች፣ ተቋማት አሉት።[16]

በተጨማሪም ከውሃ፣ ከአየር፣ ከየብስ (ከመሬት) የሚመጡ ለሕዝብ ደህንነት አስጊ የሆኑ ነገሮችን በመለየትና የመከላከያ መፍትሔ በማበጀት ከፍተኛ የሆነ የሥነ-ዕውቀት ሥርዓትና ተቋም ሆኖ ዘመናትን ተሸጋግሯል። የመድ-ዓ ሥርዓተ-ማኅበር ማናቸውም ለሕዝብ ደህንነት ጠቃሚ ወይም ስጋት የሆኑ ጉዳዮች ከአንዱ የአፋር ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ በቀላሉ ለማድረስ የሚያስችለው ልዩ የመረጃ ልውውጥ አሠራርም አለው። እሱም "ዳጉ" ይሰኛል። የተደራጀ፣ ራሱን በቻለ የሥነ-ሥርዓት ደንብ የሚመራው የዳጉ የመረጃ ልውውጥ ለሕዝብ ደህንነት ልማት ከፍተኛ መሠረት ያለው ነው።

በመድ-ዓ ሥርተ-ማኅበር የሚመራው የአፋር ሕዝብ እና አካባቢ ደህንነት ልማት ለተቀረው የኢትዮጲያ ሕዝብ ደህንነት መጠበቅ ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታል። ከቀይ ባሕር ጋር የ800 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የዳር ድንበር ጠባቂ ሕዝብና አካባቢ በመሆኑ የመድ-ዓ ሥርዓተ-ማኅበር የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት ተቋም እንደ ሀገር ከፍተኛ ውለታ ያለው ሆኖ ይጠቀሳል።

---

[14] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ መድ-ዓ (የአፋር ሕዝብ የባሕል ሕግ ሥርዓት)፣ ገጽ 63፣ ሰኔ/2010

[15] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ መድ-ዓ (የአፋር ሕዝብ ባሕላዊ ሕግ ሥርዓት)፣ ከገጽ 180-191፣ ሰኔ/2010

[16] እንደላይኛው፣ ከገጽ151-157

## 5 ማሳያ ሁለት - ገዳ የኦሮሞ ሕዝብ ባሕላዊ ሥርዓተ-ማኅበር የሕዝብ ደህንነት ተቋም

የገዳ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓትንን በሚገባ ለማወቅና ለመረዳት አምስቱን የገዳ ማዕከላትን (ኦዳ ሸነን) ማጥናትና መገንዘብ የግድ ይላል። ኦዳ-ሸነን የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

1. ኦዳ ሮባ (ማዕከሉ ባሌ፣ ጊኒር ወረዳ ይገኛል)

2. ኦዳ ነቤ (በአዲስ አበባ አቅራቢያ፣ ከዱከም በስተሰሜን ይገኛል)

3. ኦዳ ቡልቱም (ገለምሶ አቅራቢያ ይገኛል)

4. ኦዳ ቢሲል (ደቡባዊ ምዕራብ ሸዋ ውስጥ ይገኛል)

5. ኦዳ ቡሉቅ (መገኛ ሥፍራው በሚመለከት የተጣራ መረጃ አላገኘሁም) ናቸው።[17] በአሁኑ ጊዜ ግን ከዚህም በላይ እንደሆኑ ይገለፃል።

የገዳ ከፍተኛ አመራሮች (ከኦዳ ቡልቱም አኳያ) - "ሆራ-ባዱ" ተብሎ በሚታወቀው ቦታ ላይ በየስምንት ዓመቱ የሚሰበሰበው ጉባኤ የሚመርጣቸው ከፍተኛ የገዳ ሥርዓት አመራሮች የሚከተሉት ናቸው።

1. አባ-ቦኩ - የበትረ ሥልጣኑ አባት ማለት ነው። በቀኝ እጁ "ቦኩ" የተባለውን የሥልጣን ምልክት ዱላ ይይዛል። በግንባሩ "ከለቻ" ያስራል። ለቀጣይ ስምንት ዓመታት የኦዳ-ቡልቱም አባ-ገዳ ሆኖ ያገለግላል። "መነ-ቦኩ" የሚባልና የሚባሉ አመራሮችን ያዋቅራል። መነ-ቦኩ የአባ-ገዳው ጽ/ቤት ልንለው እንችላለን።

2. ሸነን-ገዳ - ጥሬ ቃሉ አምስቱ ገዳዎች ማለት ሲሆን የአባ-ቦኩ ካቢኔዎች ናቸው። እነርሱም፤

    2.1 አባ-ዱላ (የጦር ሚኒስቴር)

    2.2 አባ-ሆሪ (የኢኮኖሚ ጉዳዮች ሚኒስቴር)

    2.3 አባ-ዲዳ (የትራንስፖርት፣ የግንኙነትና የውጭ ጉዳዮች ሚኒስቴር)

    2.4 አባ-ሤራ (የሕግና የፍትህ ጉዳዮች ሚኒስቴር)

    2.5 አባ-ቢያ (የዜግነት፣ የሀገር ግዛትና የአስተዳደር ሚኒስቴር) ናቸው።

3. መነ-ሀዩ - የኦዳ-ቡልቱም ከፍተኛ አመራሮች አማካሪዎች ናቸው። አባላቱ "ሀዩ" ተብለው ይታወቃሉ። አዋቂዎች፣ ምሁራን እንደ ማለት ነው። ከዚህ ቀደም በገዳው ሥርዓት ከፍተኛ አመራርነት (አባ-ገዳ፣ ሸነን-ገዳ) ሆነው ያገለገሉ ናቸው። "ገዳ-ሞጂ" ደረጃ የደረሱ ይባላሉ።[18]

የገዳ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓተ-ማኅበር በሥልጣን ክፍፍሉ (Distribution of Powers) እንደምንመለከተው ማኅበራዊ፣ ምጣኔ-ሃብታዊ እና ፖለቲካዊ ለሆኑ የሕዝብ ደህንነቶች ጥያቄዎች ሁሉ ምላሽ የሚሰጥ ነው። በአባ-ገዳው የበላይ መሪነት የአያሌ የዘርፍ ኃላፊዎች (በዛሬው ዘመን አገላለጽ ሚኒስትሮች) ባሉት መዋቅሩ የሕዝብ ደህንነትን ያሳልጣል።

ለምሳሌም የገዳ ሥርዓት በየስምንት ዓመቱ ሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የሥልጣን ሽግግር እያካሄደ ለዓለም ፋና ወጊ ሆኖ ይጠቀሳል።[19] የሀገራችን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ እና የዓለም ክፍሎች የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር አስጨናቂ፣ ደም አፋሳሽ፣ ለሀገር እና ለሕዝብ ደህንነት አስጊ መሆኑ የሚታወቅ እውነታ ነው። ነገር ግን የገዳ ሥርዓታችን እና ሌሎችም ብዙዎች የሀገራችን ባሕላዊ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓተ-ማኅበራት በሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር የረዥም ዕድሜ ልምድ፣ አሠራር እና ዕውቀት ያላቸው ናቸው። ሆኖም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ከውጭ ያመጣነው የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ዕውቀት እና አሠራር ሠላማዊውን መንገድ አስጥሎን ደም አፋሳሹን መንገድ አሲዞን እንገኛለን። ይህ ለምን፣ እንዴት ሆነ? የሚል ጠያቂ፣ የተማረ ዜጋ ማፍራትም አቅቶን የነበረውን ችግር ሳንፈታ ወደ ሌላ ችግር እየተሸጋገርን ያለን ይመስለኛል።

---

[17] አፈንዲ ሙተቂ፣ ቦረና እና በሬንቱ፣ ኦሮሞ እና ኦሮሚያ በኢትኖግራፊ ዐይን፣ ገጽ 42፣ 2013

[18] መነ-ሀዩ የሚመረጡ አይደሉም፡፡ ከዚህ ቀደም ተመርጠው ለስምንት ዓመታት ያገለገሉ የሥራ አመራሮች፣ አባት ጡረተኞች ናቸው፡፡

[1919] እሸቱ ኢረና ዲባባ፣ የኦሮሞ ታሪክ (ከጥንት እስከ 1890ዎቹ መጨረሻ)፣ ከገጽ 144-171፣ 2001

የገዳ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት ለሁላቀፍ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት ነው። ለዚህ ሥርዓት መሠረቱ ደግሞ የዋቄፈና ባሕላዊ ሃይመናት ነው። እንደሚታወቀው በኦሮሞ ሕዝባችን ውስጥ ዋቄፈና የተባለ የሀገር በቀል ወይም ባሕል ሃይማኖት ይገኛል።[20] ሃይማኖት የአስተሳሰቦች፣ የአሠራሮችና የሥርዓታት ምንጭ በመሆኑ የገዳ ሥርዓት - ማኅበርም የሚመነጨው ከዋቄፈና ባሕላዊ ሃይማኖት ሥርዓትና ተቋም ውስጥ ነው።[21] የዋቄፈና የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሃይማኖት ከአብራሃም ሃይማኖቶች ባልተናነሰ የሥነ - ፍጥረት፣ የሥነ - ሕይወት እና የሥነ - ዓለም ጉዳዮች ሁሉ በዝርዝር የሚያስተምር የሥነ - ሃይማኖት የዕውቀት ምንጭ ሆኖ ይጠቀሳል። ስለሆነም የገዳ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት - ማኅበርን በማስገኘት ለሰው ልጅ ሕልውና መሠረታዊ የሆኑ የአስተዳደር፣ የማኅበራዊ፣ የምጣኔ - ሃብታዊ፣ የምግብ፣ የጤና፣ የአካባቢያ ሠላምና ደህንነት ወ.ዘ.ተ ጉዳዮችን ያሳልጣል።

በተለይም "ሰፉ" በተሰኘው የገዳ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት - ማኅበር ክፍሉ ሰው የልጅ ከፈጣሪው፣ ከሌሎች ፍጡራን ማለትም ከተክሎች፣ ከእንስሳት፣ ከመሬት፣ ከሰማይ ወ.ዘ.ተ ጋር እንዴት በሠላማዊና በሚደጋገፈው የተፈጥሮ ግንኙነት መሠረት ሊኖር እንደሚችል ያስተምራል።[22]

## 6 ማሳያ ሦስት - የሲዳማ - ሤራ (የሲዳማ ሕዝብ የባሕል ሥርዓተ - ማኅበር) የሕዝብ ደህንነት ተቋም)

"ሉዋ" ማለት በጥቅሉ የወንዶች ማኅበራዊ እና ፖለቲካ ሥርዓት ተቋም ነው። በሲዳማ - ሤራ ሥርዓት መሠረት አንድ ወንድ በሲዳማ ሕዝብ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችለው በሉዋ ከተሳተፈ እና ካለፈ ብቻ ነው።[23] የሲዳማ - ሤራ የማኅበራዊ፣ ምጣኔ - ሃብታዊና ፖለቲካዊ ሠላምና ደህንነቶች ከሉዋ የመሪነት የሥልጠና ተቋም ጋር በቀጥታ የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን። በሉዋ የሕዝብ መሪዎች ሥልጠና ተቋም ውስጥ ያላለፈ ሰው ምንም ዓይነት የሕዝብ አገልግሎት ኃላፊነት ሊሰጠው አይችልም። ምክንያቱም ሕዝባዊ ኃላፊነቶች የግለሰብ አቅምን፣ የብዙሃን የጋራ ትብብርንና ትስስርን (Networks) ይፈልጋሉና ነው።

የሲዳማ ሤራ የሕዝብና የሀገር ደህንነት ሥርዓት የሚመራው "ሞቴ፣ ወማ፣ ጋና፣ ጋደላ፣ ቃሪቻ፣ ጋሮ፣ ጌሎ በሚባሉ እና በሌሎች የማዕረግ ሥም ባላቸው ዋና መሪነት ነው።[24] የተለያየ የማዕረግ ሥያሜ የያዙት የተለያየ አካባቢና ጎሣ (ሕዝብ) የሚመሩ በመሆናቸው እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። የሲዳማ ሕዝብ ሥርዓት ሙሉ ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል ሥርዓት ዓይነት የተዋቀረ ሆኖ ይገኛል። ከላይ የተጠቀሱት የሕዝብ መሪዎች ለየአካባቢያቸው እና ሕዝባቸው ባለ ሙሉ ሥልጣን መሪዎች ናቸው። ከእነርሱ በላይ የሆነ ሌላ አካል የለም። የጋራ ለሆነ ጉዳያቸው ግን በጋራ ሆነው በመመካከርና በመወያየት ይወስናሉ። የጋራ ውይይቱንና ምክክሩን የሚመሩበት የራሱ የሆነ የሥነ - ሥርዓት ደንብ አላቸው።

የሲዳማ - ሤራ የሕዝብና የሀገር ደህንነት እና ልማት ሥርዓት ተቋም በውስጡ አያሌ ንዑስ የሕዝብ ደህንነት ተቋማት ይገኛሉ። ለምሣሌ የወታደራዊ ደህንነት (Military Security)፣ ያካ (የሴቶች መብቶች ጥበቃ ተቋም)፣ ሀላሌ (ከፍተኛ የሥነ - ምግባር እና የሥነ - ሥርዓት መጠበቂያ ደንብ) እና ሌሎች መጥቀስ ይቻላል።[25] በአጠቃላይ የሕዝቡ ባሕላዊ ተቋም የሰው ልጅ ለመኖር በሚያስፈልገው የሕይወት ዘርፍ ሁሉ፣ ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ፣ የተሟላ የሠላምና ደህንነት ዕውቀት፣ አሠራር፣ አመራር ሥርዓትና ተቋም ሆኖ ለዘመናት አገልግሏል። አሁንም በአገልግሎት ላይ ይገኛል።

በሲዳማ ሤራ ሥርዓት ውስጥ "ጨምበላላ" የተሰኘው የዘመን መለወጫ ሥርዓት - በዓል ብዙ ልዩ ገጽታዎች ያሉት ነው። ሥርዓት - በዓሉም በብዙ የሀገር በቀል ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ምጣኔ - ሃብታዊና አስተዳደራዊ የሕዝብ ደህንነት ዕውቀቶችና ዕሴቶች የተሞላ መሆኑንም ማስታወስ ጠቃሚ ይሆናል።

## 7 ማሳያ አራት - የአባት የሕዝብና የሀገር ደህንነት ሥርዓት ከመንዝ የአለቃ ተቋም አኳያ

በአማራ ሕዝብ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙትን የባሕል ሥርዓተ - ማኅበራት በጥቅሉ "የአባት ሥርዓት - ማኅበር" በሚል ማጠቃለል ይቻላል። በሸዋ፣ በጎንደር፣ በጎጃም እና በወሎ የተለያዩ መጠሪያ ሥም ያላቸው አካባቢያዊ ሥርዓት - ማኅበራት ቢኖሩም ለአማራ ሕዝብ ታሪካዊ፣ ባሕላዊና ሥነ - ልሳናዊ አንድነት ሲባል በአንድ የአባት ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ መመልከቱ

---

[20] ቀነኣ ለሚ ጎበና (ዶ/ር)፣ ሚቶሎጂ፣ ሃይማኖትና ገዳ፣ ገጽ 63፣ ሰኔ/2012

[21] እንደላይኛው፣ ገጽ 63 እና 67

[22] እንደላይኛው፣ ገጽ 56

[23] የሲዳማ ዞን ባሕል፣ ቱሪዝምና የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፣ የሶዳማ ብሔር ታሪክና ባሕል፣ ገጽ 186፣ የካቲት 2003

[24] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የሲዳማ ሤራ (የሲዳማ ሕዝብ ባሕላዊ ሥርዓት)፣ 2005፣ ያልታተመ

[25] እንደላይኛው::

የተሻለ እንደሆነ በማመን በዚህም መጠቀምን ተመርጧል። በዚህ ጥናት ውስጥ የምንመለከተው በአባት የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት ውስጥ የመንዝ አካባቢ ሥርዓተ-ማኅበርን ይሆናል።

በአማራ ሕዝብ፣ በአባት ሥርዓተ-ማኅበር ውስጥ የመንዝ አካባቢ የሕዝብ ደህንነት ተቋም የ"አለቃ ሥርዓት" ይሰኛል።[26] በመንዝ አካባቢ ማናቸውም የባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥራዎች ሲሠሩ የኖሩትና አሁንም የሚሠሩት በ"አለቃ ሥርዓተ-ማኅበር" አማካኝነት ነው። ይህንንም ለማመልከት አንድ የመንዝ ሕዝባዊ አባባል አለ። እሱም "ምድር በአለቃ፣ ሰማይ በጨረቃ" የሚባለው ነው። ሕዝባዊ ብሂሉ የአለቃ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓትንና ተቋም ሁለንተናዊ አገልግሎትን ያሳውቃል። ከአለቃ ሥርዓት ውጪ የመንዝ ሕዝብና ምድር ሠላምና ደህንነት ሊያገኝ እንደማይችልም ያመላክታል።

የአለቃ ሥርዓት የተለያዩ መዋቅራዊ አደረጃጀቶች አሉት። ዋናውና መሠረታዊው፣ ከላይ ወደ ታች የሚከተለውን ይመስላል፡ -

1. ምስለኔ

2. ግንድ አለቃ

3. ወገብ አለቃ

4. የቤት አለቃ

5. ምንዝር ተብሎ ይታወቃል።[27]

የመንዝ የአለቃ ሥርዓት ለሕዝብ ደህንነት ሲባል የተፈጥሮ ሃብቶችን በማልማትና በመጠበቅ፣ አለመግባባቶችን በመቆጣጠርና በመፍታት ለዘመናት የካበተ መልካም ልምድ፣ ችሎታና ሕዝባዊ አቅም ያለው ነው። በተለይም ለሕዝብ ደህንነት ዋና መሠረት የሆነውን የተፈጥሮ አካባቢያዊ ሃብትን በመጠበቅ ረገድ አስደናቂ ጥበባዊ ተቋም እንደሆነ ይነገርለታል። ለዚህም ማሳያ የጓሣ ሥረጌ ጥብቅ ልማት እስከ አሁን ያልተቋረጠ በመሆን ይታወቃል።[28] የመንዝ ጓሣ ሣር ጥብቅ ልማትና ጥበቃ ልዩ ቦታ ያለው ነው። "ምንጭ ከደፈረሰ፣ የመንዝ ጓሣ ሥረጌ ከታረሰ፣ የኑሮ ሥርዓት ፈረሰ" ተብሎ በሕዝባዊ አባባል ትምህርት ይሰጥበታል።

የተፈጥሮ አካባቢው ለሕዝቡ ደህንነት ብቻ ሳይሆን ለዱር እንስሳት ጭምር ታሳቢ ያደረገ ነው። ይህንንም በሕዝባዊ አባባል ይገለፃል። "ሥረጌዎቹ የጎልማሶች መጫወቻ፣ የዱር እንስሶች መፈንጫ ናቸው" ተብሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል።

በአጠቃላይ በየአካባቢው የነበረው የሕዝብ ደህንነት ሥርዓትና ተቋም በተናጠል፣ እንደ ሀገር ደግሞ በጋራ ሲደመር ብዙ የሀገር በቀል ወይም የባሕል የሕዝብና የሀገር ደህንነት ልማት ማካሄጃ ሳይንሳዊ ወይም ዘመናዊ ዕውቀቶች፣ ልምዶች፣ አሠራሮች፣ ሥርዓታትና ተቋማት በኢትዮጲያ ውስጥ እንዳሉን መገንዘብ ይቻላል። በቀላል አገላለጽ "ሳይንስ" ማለት "ችግር ፈቺ፣ የተደራጀ ዕውቀት፣ አሠራርና አመራር" ማለት ከሆነ በሀገር በቀል ወይም የባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት-ማኅበራት (Cultural Human Security Systems) ራሳቸውን የቻሉ የሳይንሳዊ ዕውቀት፣ ትምህርትና አሠራር ምንጭ መሆናቸውን መረዳት ይገባናል።

በአፍሪካ ደረጃ በተለይም በሀገራችን ያለው ችግር ሳይንሳዊ ዕውቀትን ከምዕራባውያን ዕውቀቶችና አሠሮች ጋር ብቻ አያይዞ የመረዳት እና የመተርጎማችን ሁኔታ ነው። ይህም የተሳሳተ የሳይንስ ዕሳቤ መሆኑ አያጠያይቅም። በሀገራችን ባሕል የሳይንስ ተቃራኒ፣ ኋላ ቀር፣ ያልተደራጀ፣ ያልተጠና፣ ያልተረጋገጠ ወ.ዘ.ተ በሚል የጥላቻ ፍርጃ (Stereotype) ተበዩኖበት እናገኘዋለን።[29] ይህ የጥላቻ ብይን ከምዕራባውያን የመጣ ቢሆንም የእኛ የአፍሪካውያን ምሁራን "አሜን" ብሎ የመቀበል ሁኔታ ይበልጥ አስገራሚና አሳዛኝ ያደርገዋል። "አሜንታ" ለሃይማኖት እንጂ ለሳይንሳዊ ዕውቀትና ትምህርት የሚጠቅምና የሚገባ አልነበረም። እኛ ግን ለሁለቱም ተጠቅመንበታል፣ እየተጠቀምንበትም እንገኛለን።[30]

## 8 የሀገር በቀል እና የውጭ ዕውቀቶችን ማስተሳሰር

---

[26] አብዱልፈታህ አብደላህ፣ በአማራ የአባት ሥርዓት ውስጥ የመንዝ አካባቢ ሥርዓተ-ማኅበር፣ 2014፣ ያልታተመ

[27] ፊታውራሪ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋሪያት በፍርዱ፣ አራዳ፣ 1990

[28] ሔኖክ ስዩም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን የቱሪዝም ማውጫ፣ ገጽ 55፣ የታተመበት ዓመት ያልተገለጸ፡፡

[29] ይድነቃቸው ከበደ እና ኢሳያስ አየለ፣ የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጲያ፣ ቅጽ 1፣ የፍሕና የሕግ ሥርዓት ኢንስቲትዩት፣ 2007

[30] እንደላይኛው፣ ገጽ 16 እና 21

የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት ልማት መሠረቱ ሀገራዊ ዕውቀት እና ባሕል መሆን እንደሚገባው የዘመናችን ሳይንስ ያስገነዝባል። የአፍሪካ ነባር ዕውቀቶች ከዘመናዊው ሳይንስ ፍልስፍና ጋር የሚሄዱ፣ ከምዕራባውያን እንደ አዲስ የምንቀዳቸው አሠራሮች በአፍሪካውያን ጥልቅ ባሕላዊ የዕውቀት ባሕር ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን ምሁራን ማስገንዘብ ጀምረዋል።

*"...በሰው እና የተፈጥሮ አካባቢ ሁለንተናዊ ደህንነት (Wellbeing) መካከል ያለውን ጥብቅ ትስስር ያሰሳያሉ። በአጠቃላይ በዘመናዊው ሳይንስ እና በሀገር በቀል ዕውቀቶች መካከል የሚፈጠር ሥልታዊ ቅንጅት ዛሬ ለተጋፈጥናቸው በርካታ ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ለማመንጨት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚያስችል ይታመናል።"*[31]

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም፣ እ.ኤ.አ በ1994 ባወጣው የሕዝብ ደህንነት ግምገማ መሠረት የሰው ልጅ ብዝሃ-ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ለመኖር የሚከተሉት ወሳኝ ነገሮች እንደሚያስፈልጉት ያስገነዝባል። እነርሱም ምግብ፣ ጤና፣ ማኅበረሰብ፣ ምጣኔ-ሃብት (ኢኮኖሚ)፣ ፖለቲካ እና አካባቢያዊ ደህንነት ናቸው። በተጨማሪም የሰው ልጅ ማንነት እና ማኅበረሰባዊ ደህንነት (Dignity and Cummunity Security) ከባሕል ጋር በጥብቅ የተሳሰሩና የተዛመዱ መሆናቸውን ያረጋግጣል።[32]

በመሆኑም የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት (Human Security) ከሀገር በቀል ወይም ከባሕል የሕዝብ ደህንነት ተቋማት ለይቶ ማሰብ የሚቻል አይደለም። የሕዝብ ደህንነት ፍልስፍናዎች፣ ዕሳቤዎች፣ ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎች፣ አደረጃጀቶችና አሠራሮች ሁሉ መነሻ መሠረታቸው የአካባቢያቸው የተፈጥሮ ሥነ-ምህዳር እና የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት ተጨባጭ ሁኔታዎች መሆን እንዳለባቸው እንገነዘባለን። ይህንን ያላገናዘበ የሕዝብ ደህንነት ልማት በጽኑ መሠረት ላይ ሊቆም ስለማይችል፣ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች በቀላሉ ሲፈርስና ሲገነባ፣ ዘላቂነት፣ አስተማማኝነት የሌለው ይሆናል።

ስለሆነም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ለሕዝብ እና ለሀገር ደህንነት ልማት የምንጠቀምባቸው ከውጭ የመጡ ፍልስፍናዎች፣ ዕሳቤዎች፣ ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎች፣ አደረጃጀቶችና አሠራሮች ወ.ዘ.ተ ከሀገር በቀል ወይም ከባሕል የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት ማስጠበቂያ ሥርዓተ-ማኅበራት ጋር ማስተሳሰር፣ ማዛመድ፣ ማጣጣም፣ ማጣመር ይኖርብናል። ይህም በተለያዩ ሳይንሳዊ መንገዶች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ነው። በዘመናችን የሳይንስ ዕውቀት የውጭውን እና የውስጡን ወይም የራስን እና የሌላውን ወይም አዲሱን እና ነባሩን ዕውቀቶች በተጠና ሁኔታ በመቀመር አልያም ጎን ለጎን በማስኬድ ወይም እንዳስፈላጊነቱ በሁለቱም መንገድ በመጠቀም መሥራት ይቻላል። በመቻልም ላይ ይገኛል። ብዙ የዓለማችን እና የአፍሪካ ሀገራት ይህንን አሠራር በብዛትና በስፋት በመጠቀም ላይ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው።[33]

## 9 የሀገር በቀል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓተ-ማኅበራት አሁናዊ ሁኔታ

ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አብዛኛዎቹ የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት እየተዳከሙ መጥተዋል። የዚህም ቀጥተኛ ምክንያት የማዕከላዊ መንግሥታት ከቅኝ ገዢዎች ወይም ከምዕራባውያን ጋር በነበራቸው እልህ አስጨራሽ ትግል የምዕራቡን ዘመናዊነት ወደ ሀገራችን ለማምጣት በነበራቸው ጽኑ እምነት የሀገር በቀሉ ዕውቀትና ሥርዓት ሊዘነጋ በቅቷል። እንደሚታወቀው ከዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ዘመን ጀምሮ የማዕከላዊ መንግሥታት በከፍተኛ የውጭ ኃይሎች ከበባ እና ማስጨነቅ ውስጥ ገብተዋል። ከዚህም ከበባና ማስጨነቅ ለመውጣት የምዕራባውያን ዓይነት ሥርዓተ-ማኅበራት ያልፈለገናል የሚል እምነትና አቋም ሊወስዱ ችለዋል። ይህም ሒደት የሀገር በቀል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓተ-ማኅበራትን በቀጥታ ሊያዳክማቸው በቅቷል።[34]

የአፄ ምኒሊክ የሀገር ግንባታ የደቡብ ኢትዮጲያ ዘመቻዎች፣ አብዛኛወቹን የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራትን በከፊል የጎዳ መሆኑ ቢታወቅም[35] ሀገርን ከቅኝ ገዢዎች የማዳን ሥራ ሠርተዋል። አፄ ኃይለ ሥላሴም ጥብቅ የሆነ የማዕከላዊ መንግሥት ሥርዓት ለመመሥረት በመሻት መጠነ ሰፊ የሆኑ የምዕራባውያን ሕግጋትና ሥርዓትን በማምጣት[36] ይታወቃሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሀገር በቀል ዕውቀትና ትምህርት ገለል መደረጉ፣ መጀመሪያ አካባቢ በውጭ ሀገራት የትምህርት አስተዳደር አመራሮች የመመራቱ ሁኔታ፣ በውጭ ፊደላትና ቋንቋ የሚያስተምር፣ ምዕራባዊ ወይም የቅኝ ገዢ ሀገራትን ማዕከል

---

[31] ፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለዘላቂ ሀገራዊ መፍትሔ፣ ገጽ 21፣ የካቲት/2013

[32] Matthew S., Global Governabce: A Review of Multilateralism and International Organizations, Oneline Publication date, 08/ march/2022.

[33] ይድነቃቸው ከበደ እና ኢሳያስ አየለ፣ ባሕላዊ ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጲያ፣ የሕግና የፍትሕ ሥርዓት ምርምር ኢኒስቲዩት፣ ቅጽ 1፣ ከገጽ 15-32/2007

[34] ታቶ ግርማ ኪዳኔ ገሊቾ (የከፋ ምክረቾ ባሕላዊ ንጉሥ)፣ ጉጀራሻ አሰፋ ዓለማየሁ ጋነቺ (የባሕል ሥርዓቱ ጠቅላይ ሚኒስትር)፣ ከተመራሻ አድማሱ አቱም አባተ (የባሕል ሥርዓቱ የከተሞች እና የጦር ሚኒስትር)፣ ነንገራሻ ሸኽ ቃሲም ሙሐመድ ሙሣ (የከፋ ምክረቾ ሥርዓት የኢኮኖሚ ሚኒስትር)፣ ሰኔ 10/2014፣ ቦንጋ ከተማ

[35] እንደላይኛው፡፡

[36] የኢትዮጲያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952፣ አንቀጽ 3347፣ 1952

ያደረገ (ኢሮ-ሴንትሪክ) የትምህርት ሥርዓት በሀገራችን መጀመሩ ወ.ዘ.ተ ለሀገር በቀል ወይም ለባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት መዳከም ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ተብሎ ይታመናል።[37]

የደርግ ዘመነ መንግሥትም “በዘመናዊ የሀገራችን ታሪክ”[38] ውስጥ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥት ሪዮተ-ዓለምን ከውጭ በማስመጣት (ሶሻሊዝም) በማድረጉ ምክንያት በሀገር በቀል ወይም በባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት ላይ ብዙ ጉዳቶች ደርሰውባቸዋል።

በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ አካባቢ የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት ዳግም የማንሠራራት ጊዜ ይሆንል የሚል ተስፋ ነበር። የማዕከላዊ መንግሥት ሥርዓት ፌዴራሊዝም መሆኑ፣ ፌዴራሊዝሙም ቋንቋን፣ ታሪካዊና ባሕላዊ ማንነትንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ፣ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 34/5 እና አንቀጽ 78/5 ላይ ለሃይማኖትና ለባሕል ተቋማት ዕውቅና ለመስጠትና መልሶ ለመገንባት ተስፋ መስጠቱ ወ.ዘ.ተ የባሕል የሕዝብ ደህንነት ስርዓቶች ዘመናቸው መጣ አስብሎ ነበር። ነገር ግን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 34/5 ለሃይማኖትና ለባሕል ዕውቅና የሚሰጠው ዝርዝር አዋጅ ይወጣል ብሎ የገባውን ቃል ሳይፈጽም የኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት በሕዝባዊ አመጽ ሊጠናቀቅ ችሏል። ነገር ግን ሕገ-መንግሥቱ አሁንም በሕይወትና በሥራ ላይ ይገኛል። እሱም በዚህ ረገድ ቃሉን ሳይፈጽም በሌላ ይተካ ይሆን? ወይንስ በ1987 ዓ.ም የገባውን ቃል አንድ ቀን ተግባራዊ ያደርግ ይሆን? የሚለው ለማወቅ አዳጋች ይመስላል።

የሀገር በቀል ወይም የባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓተ-ማኅበራት ለመዳከም ሌላኛው ምክንያት የሃይማኖት ተቋማት ሆነው ይጠቀሳሉ።[39] የሃይማኖት ተቋማት የባሕላዊ የሕዝብ ደህንነት መጠበቂያ ሥርዓተ-ማኅበራትን ማዳከማቸውን የባሕል አባቶች ያስረዳሉ።[40] በተለይም በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ደቡብ ኢትዮጲያ በስፋት የገቡ የሃይማኖት ተቋማት ባሕላዊ ሥርዓተ-ማኅበራቱን በባዕድ-አምልኮ እና በፓጋንነት በመፈረጅ ከፍተኛ የሆነ ጫና አድርገውባቸዋል።[41] የባሕል ሥርዓተ-ማኅበራት የራሳቸው የሆነ ሃይማኖት እና የሃይማኖት ክንውን (Retuals) ያላቸው በመሆኑ እነዚህን ማከናወን ባዕድ አምልኮ፣ ፀረ-ሃይማኖት፣ እምነት የለሽነት ወ.ዘ.ተ በሚል ፍረጃና ጥላቻ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል።[42]

የአብርሃም ሃይማኖቶች (አይሁድ፣ ክርስትና እና እስልምና) ለሀገራችን የሰጡት አበርክቶቶች እንዳለ ሆኖ የሀገር በቀል ወይም የባሕል ሃይማኖቶችም በአንድ ፈጣሪ የሚያምኑ፣ የሚያከብሩ፣ የሚፈሩ፣ የሚመሩ፣ በራሳቸው መንገድ ለፈጣሪ መስዋዕት የሚያቀርቡ፣ የሚያመልኩ፣ የሚጸልዩ ወ.ዘ.ተ ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌም በአብዛኛው የደቡብ ኢትዮጲያ የፈጣሪ መገለጫ ሥም ሆኖ የሚያገለግለው ዋቃ/ዋቅ በሰማይ የሚገኝ፣ የሁሉ ነገር ፈጣሪ፣ ሁሉም ዓይነት ክብርና ምስጋና የሚገባው፣ አምሳያና የሚስተካከለው የሌለው ተብሎ ይገለፃል።[43] ይህም አገላለጽ ከውጭ ከመጡት ከአብርሃማዊ ሃይማኖቶች የተለየ አንድም ነገር የለውም። ነገር ግን የእኛን አንቋሾ የውጭውን ማሞካሸት ከጥንት ጀምሮ የመጣ በመሆኑ ምክንያት እስካሁን ድረስ የሀገር በቀል ሃይማኖቶቻችን በውጭ በመጡ ሃይማኖቶቻችን አያሌ ጫና ደርሶባቸዋል። የጥንት፣ ነባር የሀገር በቀል ሃይማኖቶቻችን ችላ ማለት የተጀመረው ክርስትና እና እስልምና ከመፈጠራቸው በፊት የአይሁድ እምነት ወደ ኢትዮጲያ ሲገባ ጀምሮ ነው።[44] የአይሁድ ሃይማኖት ከክርስቶስ ልደት በፊት በኢትዮጲያ መሠረቱን ሲጥል ከፍተኛ የሃይማኖት ተወዳዳሪነት አቅም ያላቸውን የባሕል ሃይማኖቶችን ገለል ከማድረግ ጀምሯል። ይህም ኢትዮጲያን የሁሉ ነገር (የሃይማኖት፣ የሳይንስ፣ የቁሳቁስ ወ.ዘ.ተ) ተቀባይ ብቻ እንድትሆን ያደረጋት መነሻ ጉዳይ ሳይሆን እንዳልቀረ ይታመናል። ነገር ግን ኢትዮጲያ ከመቀበል ይልቅ ሰጪም እንደነበረች፣ መሆን የሚያስችላት የሃይማኖት፣ የዕውቀትና የቁስ መሠረት እንዳላት የሚታወቅ ነው። ለዚህም ሙሴን ወይም ነቢዩላህ ሙሣን ያስተማረው ኢትዮጲያዊው ዮቶርን፣ በጥንት ግሪካዊ ፈላስፋ ስለ ኢትዮጲያውያን የተጠቀሰው አገላለጽ፣ በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተገለጸው የፍትሕ ሀገርና ሕዝብነት (ፍትሕ

---

37 የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም፣ ሐዲስ ዓለማየሁ፣ ከገጽ 110-112፣ 1948

38 የደርግ ሶሻሊዝም፣ የመጀመሪያው ከውጭ የመጣ የመንግሥት ሪዮተ-ዓለም አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ከሳይንሳዊ ታሪክ አኳያ መሠረት ባይኖረውም የሀገራችን የሰለሞናዊ መንግሥታት ታሪክ ውስጥ ጉልህ ቦታ ያለው የመጀመሪያው ምኒሊክ ሪዮተ-ዓለም ከውጭ (ከእስራኤል) የመጣ እንደሆነ በክብረ-ነገሥት አንብቦ መረዳት ይቻላል፡፡

39 አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የድራሼ ወረዳ ሕዝቦች የባሕል ሕግ ሥርዓት፣ ገጽ 293 እና 294፣ ጥር/2010

40 ማካ ቱለዮ ካባ ካቴ፣ የሞሲዬ ሕዝብ ሥርዓት (ዎካቻ)፣ በዳማው (ባሕላዊ ንጉሥ) ሥር፣ እንደ ዘመናችን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የሚያገለግሉ፣ የ70ዎቹ ዓመታት ዕድሜ ባለጸጋ፣ በ209 ዓ.ም፣ ቡሳ-ቂላ ቀበሌ፣ ቂላ ከተማ

41 ተስፋጽዮን ደለለው (ዶ/ር)፣ ከሚሽንግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ (ሕይወቴ ትምህርት ቤቴ)፣ ከገጽ 68-70፣ 2007

42 ቀነኣ ለሚ ጎበና፣ ሚቶሎጂ፡ ሃይማኖትና ገዳ፣ ገጽ 62፣ ሰኔ/2012

43 እንደላይኛው ገጽ 65

44 ስርግው ገላው፣ ክብረ ነገሥት፣ ግዕዝና አማርኛ፣ የኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርቲ፣ ገጽ 19፣ 1994

ከፈጣሪ ሃይማኖት የሚመነጭ መሆኑን ልብ ይሏል) ፣ ሳይንስ የኢትዮጲያ የሰው ልጅ ምድረ-ቀደምትነት ማረጋገጡ ወ.ዘ.ተ ኢትዮጲያ ሰጪ እንጂ ተቀባይ ብቻ እንዳልነበረች፣ እንዳልሆነች፣ መሆንም እንደማይገባት የሚያረጋግጡ እውነታዎች ናቸው።

## 10 የሀገር በቀል ወይም የባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት-ማኅበራት የማንሠራራት ጅማሮ

ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በመንግሥት ፖሊሲዎች እና በሚሻሻሉ ሕጎች ውስጥ፣ ብዙ ውሱንነቶች ቢኖርባቸውም የባሕል ተቋማትን ለማካተት ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው።[45] በየአካባቢው ለብዙ አስርተ-ዓመታት ፈርሰው የነበሩ የባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት-ማኅበራት መልሰው በመመሥረት ላይ ይገኛሉ። ለምሣሌ የከፋ ምክረቾ የሀገር በቀል ሥርዓት-ማኅበር ተጠቃሽ ነው። የከፋ ሕዝብ ባሕላዊ የሕዝብ ደህንነት ሥርዓት-ማኅበር የሚከተሉት ዋና ዋና ዘርፎች ያሉት ነው።

1. ታቶ፡- ሥልጣኑ በሕግ የተገደበ ንጉሥ (Constitutional Monarchy)

2. ጉጀራሻ፡- የሚኒስትሮች አዛዥ ወይም ጠቅላይ ሚኒስተር

3. ከተመራሻ፡- የከተማና የጦር ሚኒስተር

4. ሾደራሻ፡- የአስተዳደር ጉዳዮች ሚኒስተር

5. ሌሎችም የተለያዩ ዘርፎችና መሪዎች ይይዛል።

ይህ ከፍተኛ የምክረቾ ሥርዓት ከ1889 ዓ.ም ጀምሮ ለ119 ዓመታት ፈርሶ ቆይቷል። በ2008 ዓ.ም መልሶ በሕዝቡ ተቋቁሟል።[46] ቢሆንም ግን የቀድሞ የሥራ ማስኬጃ የኢኮኖሚ ምንጩ ስለተቋረጠ ሥራውን በሚገባ ማካሄድ አልቻለም። በቀጣይ ከመንግሥት ጋር ሊኖረው የሚችለው የመደጋገፍና የትብብር ሥራ፣ አዲስና ዘመናዊ የገቢ ማስገኛ መንገዶችን ማደራጀት ይጠበቅበታል። ይህም እስኪሆን ድረስ በግላቸውና በፍቃደኛ ተባባሪዎች ድጋፍ የሥርዓት-ማኅበሩ ሥራዎች ተጀምረዋል።[47]

## 11 ማጠቃለያ

የጥንታዊት ኢትዮጲያ ሕዝቦች እንደ ሕዝብ እና ሀገር ሕልውናቸውንና ደህንነታቸውን ጠብቀው የኖሩትና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ ለዛሬ የደረሰው በሀገር በቀል ወይም በባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓትና ተቋማት መሠረትነት እንደሆነ የተረጋገጠ ነው።

ስለሆነም ነባር የሕዝብና የሀገር የዕውቀት ክምችቶችን (Capital of knowledge) ከዘመናዊ የሳይንስ ዕውቀት ጋር አጣጥሞ መጠቀም ትክክለኛው የሳይንስ መንገድና አሠራር መሆኑን መረዳትና ማስረዳት ይኖርብናል።[48] የሀገራችን በአጠቃላይም የአፍሪካ ዋነኛ ችግር በራሳችን የዕውቀት ሃብት (Capital of knowledge) ዙሪያ ጥናትና ምርምር አለማካሄዳችን፣ በውጭ ዕውቀትና አሠራር ላይ ጥገኛ መሆናችን እንደሆነ፣ ይህም ለብዙ አደጋዎችና ፈተናዎች እያጋለጠን መሆኑ እየታመነበት ይገኛል።[49]

በተለይም የሕዝብና የሀገር የደህንነት ተቋማት በውጭ ፖሊዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የዕውቀት አሠራሮች፣ አደረጃጀቶችና መንገዶች ላይ ብቻ መንጠልጠላቸው ከሕዝብና ከሀገር ደህንነት አንፃር ከፍተኛ አደጋና ስጋት እንዳለው ለመገንዘብ መመራመርን አይጠይቅም። በመሆኑም በውጭ የደህንነት ስጋቶች በቀላሉ ሊገመቱ፣ ሊታወቁ በማይችሉ የሕዝብ ወይም ባሕላዊ አሠራሮችን በተጨማሪነት፣ በተጠባባቂነት፣ በአማራጭነት መጠቀም ምን ያህል ትልቅ እስትራጂያዊ ዋጋ እንዳለው የጥናቱ ዋንኛ ማጠቃለያ ሀሣብ ነው።

---

[45] የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ፣ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ የካቲት 25/2003

[46] ታቶ ግርማ ኪዳኔ ገሊቾ (የከፋ ምክረቾ ባሕላዊ ንጉሥ)፣ ጉጀራሻ አሰፋ ዓለማየሁ ጋነቺ (የባሕል ሥርዓቱ ጠቅላይ ሚኒስትር)፣ ከተመራሻ አድማሱ አቱም አባተ (የባሕል ሥርዓቱ የከተሞች እና የጦር ሚኒስትር)፣ ነገገራሻ ሸኽ ቃሲም ሙሐመድ ሙሣ (የከፋ ምክረቾ ሥርዓት የኢኮኖሚ ሚኒስትር)፣ ሰኔ 10/2014፣ ቦንጋ ከተማ

[47] እንደላይኛው፡፡

[48] ፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለዘላቂ ሀገራዊ መፍትሔ፣ ከገጽ 19-23፣ የካቲት/2013

[49] ይድነቃቸው ከበደ፣ ኢሳያስ አየለና ገ/መስቀል ገ/ዋህድ፣ የባሕል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጲያ፣ ቅጽ 1፣ የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢኒስቲቱት፣ ገጽ 21፣ 2007

የሀገር እና የሕዝብ ደህንነት አንዱ ጥንካሬ ሊሆን የሚችለውና የሚገባው የተለያዩ አማራጮችን እና ዕድሎችን መጠቀም መቻሉ ነው። የተለያዩ አማራጮችና ዕድሎች ሲባል ደግሞ በሰፊው ትርጉሙ መሆን ይኖርበታል። ይህም ከውጪው እስከ ሀገር ውስጡ ወይም ከሳይንሱ እስከ ባሕሉ አማራጭና ዕድል የሚለው ዳራ መያዝ አለበት።

ለሀገር በቀል ወይም ለባሕል የሕዝብ ደህንነት ሥርዓታችንና ተቋሞቻችን ምክረ-ሀሣቦች፡-

1. የጥናትና ምርምር ሥራዎች - በሀገር በቀል ወይም የባሕል የሕዝብ ደህንነት ስርዓቶች ዙሪያ ሰፊ የጥናትና ምርምር ሥራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል። የሀገር በቀል የሕዝብ ደህንነት ዕውቀቶች፣ ፍልስፍናዎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አደረጃጀቶች፣ አሠራሮች፣ ውጤታማ ልምዶች ወ.ዘ.ተ ማጥናት የዘመናዊነት፣ የሳይንስ እና የሥልጣኔ ዋንኛ ምልክት ነው።

2. አውደ ውይይቶችና ሥልጠናዎች - ባሕላዊ የሕዝብ ደህንነት ተቋማትን መጠቀም ያስፈልጋል? ወይንስ አያስፈልግም? ያስፈልገናል ከተባለስ በምን አግባብ? በምን ሁኔታ? በምን ደረጃ? በምን ሕግና ሥርዓት? በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ አውደ-ውይይቶች፣ ምክክሮችና ሥልጠናዎች መካሄድ ያስፈልጋቸዋል። በቂ ውይይቶች ሳይከናወኑ የሚከናወኑ አሠራሮች ብዙ ጉድለትና ችግር ማስከተላቸው የሚታወቅ ነው።

3. ለሀገር በቀል ወይም ለባሕል የሕዝብ ደህንነት ተሟሏት የሕግ ዕውቅና መስጠት - ከ1987 ጀምሮ በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 34/5 እና አንቀጽ 78/5 ለባሕል ተቋማት ዕውቅና እንደሚሰጥና መልሰው የማደራጀት ሥራ እንደሚሠራ ደንግጓል። በዚህም መሠረት የተለያዩ ሙከራዎችና ጥረቶች ተከናውነዋል። ለምሣሌ አንዳንድ ክልሎች ለባሕል ተቋሞቻቸው ዕውቅና የመስጠትና የማደራጀት አዋጅ አውጥተው በሥራ ላይ ይገኛሉ። ኦሮሚያን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን በፌዴራል ደረጃ ወጥ የሆነ ሥራና ተግባት ገና አልተጀመረም። ሁሉም ክልሎች መሰሉን ሥራ ሠርተው በሀገር ደረጃም የጋራ ምክር ቤት በሚመሠረትበት መንገድ መመራት ያስፈልገዋል። መሰሉ ልምድ በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ይገኛል።

4. የትምህርት ሥርዓታችን መነጽር መቀየር - የሀገራችን የትምህርት ሥርዓት ከዘመናዊነት፣ ከሳይንስ እና ከሥልጣኔ ትክክለኛ ትርጓሜ አንፃር ዘመናዊ፣ ሳይንሳዊና ሥልጡናዊ ያልሆነ እንደሆነ በብዙ ምሁራን ይተቻል። የነገሮች አረዳድ፣ አተረጓጎምና አገላለጽ እንደ ሀገራዊ አውድ መረዳት፣ መተርጎም እና መግለጽ የማይችልና የማያስችል፣ ሁሉም ነገር በውጭ፣ በሌላ ሀገርና ምሁራን እንደተረዱት፣ እንደተረጎሙትና እንደገለጹት ይዞ የሚጓዝ፣ ሳይንስን እንደ እምነት ወይም ሃይማኖት በመቀበልና በሰበካ በማስፋፋት ላይ የተመሠረተ የሚያደርግ አሠራር ነው ተብሎ ይነቀፋል።[50]

   ትክክለኛው የዕውቀት ምንጭና መንገድ ውስጣዊ፣ ሀገር በቀላዊ፣ ባሕላዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ አካሄድ ነው ተብሎ ይታመናል።[51] ስለሆነም ዘለቄታዊ የሕዝብ እና የሀገር ደህንነት ከሚገኝባቸው መንገዶች አንዱ፣ ምናልባትም ዋንኛው የትምህርት ሥርዓታችን ትክክለኛው የሳይንስ ዕውቀት፣ አሠራርና ልምድ ላይ እንዲመሠረት ማድረግ ነው። እሱም ከሀገር በቀል ወይም ከባሕላዊ ዕውቀቶች፣ አሠራሮችና ልምዶች መነሳት መቻል ማለት ነው። ይህም በተለያዩ ሳይንሳዊ አማራጮች (በማዋሀድ ወይም ጎን ለጎን ወይም በሁለቱም መንገድ) በመጠቀም ነባሩንና ከውጭ የመጣውን ማስታረቅ፣ ማመጋገብ፣ ማስተሳሰር፣ እንዲደጋገፉ ማድረግ እንደሚቻል፣ እንደሚገባም ምክረ-ሀሣቡ ያስምርበታል።

## ዋቢ መጽሐፍት


Shahrabanou Tadjbakhsh and Anuradha M. Chenoy, Human Security concepts and implications, 2007

Alula Pankhurst and Getachew Assefa, Grass-roots Justice In Ethiopia, The Contiribution of Customary Dispute Resolution, 2008

Matthew S., Global Governabce: A Review of Multilateralism and International Organizations, Oneline Publication date, 08/ march/2022.

ሐዲስ ዓለማየሁ፣ የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም፣ 1948

የኢትዮጲያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፍትሐ ብሔር ሕግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952፣ 1952


[50] ሐዲስ ዓለማየሁ፣ የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም፣ ከገጽ 110-112፣ 1948

[51] እንደላይኛው::

ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ ምቀል፣ ዝክረ ነገር፣ 2ኛ ዕትም፣ 1962

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ዐፄ ምኒሊክ እና የኢትዮጲያ አንድነት፣ 1983

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት፣ 1987

ፊታውራሪ ገብረ ሕይወት ወልደ ሐዋሪያት በፍርዱ፣ አራዳ፣ 1990

ስርግው ገላው፣ ክብረ ነገሥት፣ ግዕዝና አማርኛ፣ የኢትዮጲያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርቲ፣ 1994

እሸቱ ኢረና ዲባባ፣ የኦሮሞ ታሪክ (ከጥንት እስከ 1890ዎቹ መጨረሻ)፣ 2001

የሲዳማ ዞን ባሕል፣ ቱሪዝምና የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ፣ ሲዳማ ብሔር ታሪክና ባሕል፣ የካቲት/2003

የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ፣ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ፣ የካቲት 25/2003

ገብሬ ይንቲሶ፣ ፈቃደ አዘዘና አሰፋ ፍስሃ፣ ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጲያ፣ የኢትዮጲያ የግልግል ዳኝነት የማስማማትና ዕርቅ ማዕከል፣ 2004

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ የመጀመሪያ ዕትም 1951፣ 3ኛ ዕትም 2005

ይድነቃቸው ከበደ እና ኢሳያስ አየለ፣ ባሕላዊ ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጲያ፣ የሕግና የፍትሕ ሥርዓት ምርምር ኢኒስቲዩት፣ ቂጽ 1፣ 2007

ተስፋጽዮን ደለለው (ዶ/ር)፣ ከሚሽንግዳ እስከ ዓለም ዳርቻ (ሕይወቴ ትምህርት ቤቴ)፣ ከገጽ 68-70፣ 2007

ፕ/ሮ ላጲሶ ጌ ድሌቦ፣ የኢትዮጲያ የታሪክ መነሻና ሒደት ከዘመነ ሜጋሊቲዝም እስከ ሪፐብሊክ፣ ከ15,000 ዓ.ዓ እስከ 2000 ዓ.ም፣ 2008

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ ሔራ (የሀረሪ ሕዝብ የባሕል ሕግ ሥርዓት)፣ 2008

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ ጭሙንታንታ-ሤራ (የቡርጂ ብሔረሰብ የባሕላዊ ሕግ ሥርዓት)፣ ጥር/2008

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የድራሼ ወረዳ ሕዝቦች የባሕል ሕግ ሥርዓት፣ ገጽ 293 እና 294፣ ጥር/2010

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የሀገረሰብ የአስተዳደር፣ የሕግ እና የፍትሕ ስርዓቶች በኢትዮጲያ፣ ቅጽ 1፣ ሐምሌ/2010

ቀነኣ ለሚ ኀበና (ዶ/ር)፣ ሚቶሎጂ፥ ሃይማኖት እና ገዳ፣ ሰኔ/2012

ፕሮፌሰር መብራቱ፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ፣ ለዘላቂ ሀገራዊ መፍትሔ፣ የካቲት/2013

አፈንዲ ሙተቂ፣ ቦረና እና በሬንቱ፣ ኦሮሞ እና ኦሮሚያ በኢትኖግራፊ ዐይን፣ 2013

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የደጃዝማች ዑመር ሰመተር ለኢትዮጲያ ነፃነት የተጋድሎ ታሪክ፣ 2015

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የሲዳማ-ሤራ የባሕል ሕግ ሥርዓት፣ 2005፣ ያልታተመ

አብዱልፈታህ አብደላህ፣ የኢትዮጲያ ባሕላዊ ሥርዓተ-ማኅበራት ማውጫ፣ ቅጽ 2፣ 2014፣ ያልታተመ

ሔኖክ ስዩም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን የቱሪዝም ማውጫ፣ የታተመበት ዓመት ያልተገለጸ